ጻዲቁ እብድ

መንፈሳዊሰብከቶች ፣ ልብወለዶችና ግጥሞች

ይድነቃቸው አዲሱ

ሰኔ 2017 ዓ.ም
አዲስ አበባ

መታሰቢ ያ ነ ቱ

" ለካራ መሰቀለ ሰላም ቅድሰት ሥላሴቤተክርሰቲያንለሆነው ለማኅበረ ሥላሴ ይሁንልኝ።"

ተዘከሩኒ:በጸሎትክሙ:ወመሐሩኒ:በትንብልናክሙ:ለምሰኪን:ወለኃጥእ:ገብርክሙ:ገብረ:ማርያም

ማውጫ

1, ጳዲቁ እብድ (3)
2, መዝሙረ ዓለም (19)
3, ዝምታ (21)
4, ውሀ ና እሳቱ (22)
5, የታመነ ነው (23)
6, ፍቅር የለው ታሪኬ (24)
7, የኔ አገልግሎት (25)
8, ሰሜታዊ አገልጋይ (29)
9, የቅዱሳን ወርቃማ አባባሎች (30)

ጻዲቁ እብድ 2017 አዲስ አበባ

መኖር የሚለካው በስጋዊ ማግኘት ማጣት ውስጥ እንደሆነ የምናስብ ሰዎች ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከማንም በላይ ምስኪኖች ነን እንደሆን ይመክረናል። ምክንያቱም አለመኖር የሚባለውን ጓዝ እንደተሸከምን መርሳታችን ከዝቅታም በላይ ዝቅታ ሚሆን ከወዴት ይመጣል...?

" ስንቅ የለኝ ለላይኛው ቤቴ
ከንቱ ሁኛለው በፈራሽ ሰውነቴ"   እንዳለ ገጣሚ።

ዕለቱ ሰንበት ነው፤ ሰንበተ ክርስቲያን። ከምንም ዕለት በላይ በቤተክርስቲያናችን ትልቅ ሰፍራ የሚሰጠው ቀን ሰንበት ይባላል፤ በዚህ ዕለትም በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከታሪክም ሚልቅ በህሊናችን ሰሌዳ ሊፃፍ የሚገባው የትንሣኤያችን በኩር ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ ተስፋችንን የቀጠለበት ውዷ ስጦታችን ሰንበተ ክርስቲያን ናት። ድቅድቁ ጨለማ በብርሃን ተተክቶ ተራውን ለንጋት ለቋል፤ ምዕመናን ከመዐዛ ጥዑመ ቅዳሴ ሱታፌ አድርገው ለሳምንቱ እንዲያደርሳቸው ደጁን በመሳለም ወደየቤታቸው ያቀናሉ። ጽዮን እና ሕይወት የቤተክርስቲያኑን መግቢያ በሩን እየሳሙ ሳለ ከቤተክርስቲያኗ አንፃር ሁኖ አንድ እብድ ከፍ ባለ ድምፅ ቃላት ይወረውራል፤ ጻዲቁ እብድ ነበር...

"ወደው አይስቁ አለ ዮሐንስ ወንጌላዊ
ሰማይ ነው ቤትህ ሲባል ሰው ሲሆን ምድራዊ"

በምርጫ ስሜት ንግግሩን ከራሱ ጋር እየቀጠለ ነው፤ " እእእ... ምን አልሺኝ ነብሴ ? ምንም !" በቁጣ አንዳች ነገር እንዳጣ ክርክሩን ይቀፅላል። " እንዴት ምንም ትይኛለሽ ነብሴ ! ብርሃን ከልብ እንደሚወጣ ጨለማም ከስጋዊ ስራ እንደሚገኝ ፣ ብርሀን ማለት እግዚአብሔርን መፍራትና

ማመን ሲሆን ጨለማ ማለት ደግሞ እግዚአብሔርን አለመፍራት ና አለማመን ነው፤ ነፍስ የምትወደውን ስጋ አይወደውም ፣ ስጋ የሚወደውን ነፍስ አትወደውም ስለዚህ ሁለቱ ነፍስና ስጋ እርስ በእርሳቸው ይጣላሉ.. እም ቆይ ቆይ ... ነፍስ ልትሰራው የማትወደውን ስጋ ሊሰራው ይወዳል፣ ስጋ ሊሰራው የማይወደውን ነፍስ ልትሰራው ትወዳለች፤ አሀሀሀ..ሀሀሀሀ" ከራሱ ጋር ር ይስቃል። ወ/ሮ ጽዮን በቆመችበት በሃሳብ ተማለች..ሕይወት ልጁ ትጣራለች " እማዬ..እማዬ.." በትካዜ የሄደችዋን እናቷን ከሀሳቧ እየቀሰቀሰች፤ ጽዮን ከቁጭት ቁዘማዋ እየነቃች "እ.. ልጄ ምን አልሺኝ ? ልጅ ህይወት በእናቷ ግራ በመጋባት "ስጠራሽ እኮ አልሰማ አልሺኝ እማ.. ለምንድነው ሁሌ ይሄን እብድ ባየሽ ቁጥር በሀሳብ የምትሄጂው ? ጽዮን የልጇን የዘውትር መጠይቅ ዛሬ መመለስ እንዳለባት ተሰማት " እ.. ነይ ወደ ቤት እንሂድ እዛ እነግርሻለሁ" ጽዮን በስስት አሻግራ እያየችው ወደቤታቸው አቀኑ። ፃዲቁ እብድ ንግግሩን ተያይዟል " አይይይ ሕይወት መባዘን ..ዝም ብሎ መባከን" በቁጭት ይተነፍሳል...

ተይ ነብሴ ግድ የለም መዝኚ

ይብቃሽ ዓለምን አትመኚ

..እእእ

ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየኝ ማነው

እያለ ይዘምራል ሰው ደፋር ነው

በጉባኤ በምሽቱ የለኮሰው ጧፍ ድምቀት ከመሰለው

መከራ መሸከም ትርጉሙ እንደሆነ ማን በነገረው

እህህ.. ያማል ይታያል

በጎቹ ከመንጋው ቁጥራቸው ቀንሷል

አይዞህ እያሉ እረኞች ለበጉ የትም ይብላ ብለው ደረቅ ሳር አስጋጡት

በመሰለው እንደሚፈልጉት ሂዶ በዓሉ ከተመ ለምን ብሎ ሳይጠይቅ

ለሞት እንደሰጡት

..እህ አአአ " ፃዲቁ እብድ ቤተክርስቲያኗን አሻግሮ በናፍቆት እየተመለከተ...

እነ ሕይወት ቤት...

ህይወት በጉጉት የእናቷን ጽዮንን አይን እየተመለከተች "እማዬ ግን ቅድም እንደዛ ሀሳብ ውስጥ የከተተሽ አብድ ቆይ ማነው ነፍስ ካወኩ ጊዜ አንስቶ ሁሌ ስጠይቅሽ ስታድጊ እነግርሻለው እያልሽ ይኸው 23 ዓመት ሞላኝ ቆይ ከእኛ ጋር የሚያገናኘው ነገር ምንድነው ? ጽዮን ጊዜው እንደደረሰ በመረዳት "አይ ልጄ ዛሬ እንዲህ ሰው የመሆኔ አባትሽ ከነበረበት ጨለማ ውስጥ ወጥቶ እንዲህ ያማረ ትዳር ዛሬ ላይ ኑሮን አንቺን የመውለዳችን ምክንያት ያ እብድ ያልሺው አብድ የመሰለሽ ሰው ነው" ጽዮንን ከባለቤቷ ጋር ለጋብቻቸው ዕለት የተነሱትን ፎቶ በእጇ ይዛ የኋሊት በህሊናዋ መዝገብ እየበረረች... " ህይወት ግራ በመጋባት ስሜት ሁና "አልገባኝም እማዬ" ጽዮን ንግግሯን እየቀጠለች "ይኸውልሽ የኔ ልጅ በደንብ አድምጪኝ" ጽዮን ፎቶውን እንደያዘች በሃሳብ ስትጓዝ ህይወት የእናቷን አይን እያየች በጉጉት አብረው በጊዜ ወደ ኋላ ይመለሳሉ።

በ1990 አዲስ አበባ ስም ያልተገለፀ ቤተክርስቲያን...

እሑድ ከቀኑ 11:00 ዮሐንስ የአሁኑ ፃዲቁ አብድ ወደ ሰንበት ት/ቤት ሊገባ የቤተክርስቲያኑ አጥር እየተሳለመ ወደ ግቢው ሊገባ ሲል ከኋላው አንዲት ሴት ጠራቺው " ወንድም.... የኔ ወንድም" ጽዮን ነበረች፤ በፍርሀት እና በመሸማቀቅ ስሜት ሁና እየተጠጋቺው።ዮሐንስ ድምፁን ወደሰማበት አቅጣጫ እየዞረ "አቤት እህቴ ምን ልርዳሽ" በትህትና

ጽዮንን እየተመለከተ.. ጽዮን በተሰበረ መንፈስ እንዲህ ትለዋለች " እኔ መግባት ስለማልችል ነው እባክህ ይሄንን ጣፏ ለቤተክርስቲያን ስጥልኝ" ጧፍ የያዙ እጆቿን ወደ እሱ እየዘረጋች አንገቷን ሰብራ.. ዮሐንስ በሁኔታዋ በመገረም "ለምንድን ነው መግባት ማትችይው እህቴ ? ቤተክርስቲያን የሁሉም እናት ናት ልጇ እንዳይመጣባት ምትፈልግ እናት አለች እንዴ? በእርግጥ ከመቀድስ እንዳንገባ ምንከለከልባቸው ምክንያቶች አሉ ነገር ግን የቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ ለመግባት ምንም አያግደንም" በማለት ጽዮንን ለማጽናናት የንግግር ጉዞውን "ሀ" ብሎ ጀመረ፤ ጽዮንም በመጨናነቅ በእንባ የጠወለጉ አይኖቿን ወደ ዮሐንስ በቀስታ እያስለመለመች "እባክህ ይሄንን ብቻ ስጥልኝ ምንም አጠይቀኝ" ብላ እያነባች ጧፉን ከሰጠቺው በኋላ ስትሄድ የዮሐንስ እግሮች ከትንሽ ማንገራገር በኋላ አቅጣጫ እየቀየሩ የሰጠቺውን ጧፍ እና ነጠላውን አውልቆ ለሚገባ የሰንበት ተማሪ አዳጊ እንዲያስገባ ከሰጠ በኋላ ዞሮ ተሳልሞ ጽዮንን ወደ ምትሄድበት ይከተላት በመንገዱ ላይ እርምጃውን ተያያዘው...

እነ ጽዮን ቤት ቅያስ ውስጥ...

ምሽት 12:50 ሆኗል፤ ዮሐንስ ዳግም የጽዮንን መውጣት ከበሯ ባሻገር ሁኖ የቤቷን በር በሩቅ እየቃኘ ነው። ጽዮን ከቤቷ ተኳኩላ ወጣች፤ ዮሐንስ ይከተላትና መጨረሻ ላይ አስፓልት ዳር ላይ ያሉትን እንደእሷ የሚሰሩትን ሴቶች ሰላም ብላ አብራቸው አስፓልት ዳር ስትቆም ከሩቅ ያያትና የሹራብ ኮፍያውን አድርጎ መጥቶ አውርቷት ይወስዳታል።

እነ ዮሐንስ ቤት ውስጥ...

ዮሐንስ በውርስ የተሰጠውን የአባት እና የእናቱ ማስታወሻ ቤት ውስጥ ከጽዮን ጋር ሁነው ሳለ ጽዮንን በለሰለሰ ድምጿ ዮሐንስን ትጠራዋለች " ና እንጂ ለምን እሱ ጋር ቆምክ ደግሞ ለምንድነው ጀርባህን የሰጠኸኝ ? " ፊቱን ከተቀመጠችበት ሁኗ እየፈለገች መሆኑ ነበር፤ የዚህን ጊዜ ዮሐንስ አድርጎ የነበረውን ኮፍያ እያወለቀ ፊቱን እያዞረ "እንዴት ነሽ እህቴ" ጽዮን በመደናገጥ ስሜት " አንተ ቅድም..." ዮሐንስ የጽዮንን መደናቀጥ በመመልከት "አዎ እኔ ነኝ እህቴ ተረጋጊ" ይላታል ጽዮን ከተቀመጠችበት እየተነሳች "ይሄ እኮ ለአንተ አይመጥንህም እባክህ ከዚህ በላይ ሀጢአቴን አታብዛው" እንባ እያቀረራት... ዮሐንስ ያዘነ ፊቷን ለመፍታት እየሞከረ " ተረጋጊ እህቴ እኔ እንደምታስቢው አይነት ነገር ልፈፅም አይደለም ቅድም አዝነሽ ቤተክርስቲያኑ ጋር ሳይሽ አንድ ነገር እንደሆንሽ ገብቶኝ ነው ከዛም እስከ ቤትሽ ድረስ ተከትዬ ከቤትሽም ስትወጪ ተከትዬሽ ከዛም ወደዚህ ቤት አመጣሁሽ" በማለት ሁኔታውን ይገልፅላታል ጽዮን በሁኔታው ግራ በመጋባት "ለምን ቤት እኮ የምጦራት ታማሚ እናት አለቺኝ ካልሰራው እሷን ማኖር አልችልም እባክህ አሁን ልሂድበት ህመሜን ከዚህ በላይ እንዲሆን አታድርግ" ብላ ልቶጣ ስትሞክር ዮሐንስ በማረጋጋት "እባክሽን እህቴ ተረጋግተሽ አድምጪኝ ለእናትሽም መድሀኒት መግዣ እኔ እሰጥሻለሁ ግን ከዚህ ህይወት መውጣት አለብሽ ይሄን ህይወት ፈልገሺው እንዳልሆነ አውቃለሁ እኔም ወደ ቤቴ ያመጣሁሽ ለምታስቢው ነገር አይደለም እባክሽን ... ከቅድሙ በበረደ ንግግር ሁና ጽዮን "እንዴት እሺ ዛሬ አንተ ሰጠኸኝ እንበል ነገስ ? ደግሞ የቤት ኪራይ ፣ የምግብ ከየት አመጣለሁ እ ? ዮሐንስ ወደ እሱ ሃሳብ እየመጣች እንደሆነ በመረዳት " ከየትም ማምጣት አይጠበቅብሽም ከዚህ በኋላ ይሄ የአንቺም ቤት ነው፤

ነገ እናትሽን አምጥተናቸው እዚህ አንድ ላይ መኖር እንችላለን" ጽዮን በዮሐንስ ሃሳቧ ቢያጋድልም "አይ አልችልም ላስቸግርህ አልፈልግም" በማለት ዳግም እንዲጠይቃት በመጋበዝ ውስጧ እየዳዳ..
ዮሐንስ ንግግሯን ለማሸነፍ "ቆይ ስለምን ማስቸገር ነው ምታወሪው እባክሽ እህቴ ይሄ ቤት እናት እና አባቴ ከማረፋቸው በፊት የሰጡኝ ቤት ነው፤ የሰጡኝም ብቻዬን ሁሉን ረስቼ እንድኖር አይደለም ወንድም እህቶቼን እንዳስጠጋ ጭምርም ነው እንቢ አትበይኝ እህቴ... እንደ ወንድምሽ ተመልከቺኝ አሁን አረፍ በይና ሁሉንም ንገሪኝ ለምንድነው ወደዚህ ህይወት የገባሺው እስቲ ተረጋግተሽ ሁሉንም ነገር ንገሪኝ ከአንድ ስጋ ባንወለድም የአንድ የእግዚአብሔር ልጆች እኮ ነን ስለዚህ እህቴ ንገሪኝ" በማለት የዕረፍት ቃል ይሰጣታል። ጽዮንም እንኳን ንገሪኝ ተብላ እንዲሁም ሰሚ ምትፈልግ ነብስ ነበረችና ከመጀመሪያው ጀምራ ትምህርቷን ከ11ኛ ክፍል አቋርጣ እንዴት ወደዚህ እንደገባች ፣ ህልሟ ምን እንደነበር በእንባ ጎርፍ ትተነፍሰው ጀመር፤ ዮሐንስም አብሯት ሲያዝን እና ሲያፅናናት ከቆዩ በኋላ...ነግራው ስትጨርስ እግሩ ላይ ወድቃ እንዴት አድርጌ እንደማመሰግንህ አላውቅም ስንት ዓመት ሙሉ ሳነባ የድንግል ማርያም ልጅ ጩኸቴን ሰማኝ በ...ጣም ነው ማመሰግነው" እየተንሰቀሰቀች የሰ'ው ርሃቧን ገለፀችለት፤ ወትሮ ምስጋና የማይከጅለው ዮሐንስ " እባክሽ እህቴ ተነሺ እኔ ምንም አላደረኩልሽም በመሐሪው አምላክ ተነሺ የኔ የሆነ ምን አለኝ ሁሉ የእርሱ እኮ ነው እህቴ ! ተነሺ እባክሽ" አብሯት በደስታ እያነባ ትከሻዋን ይዞ ያስነሳታል። ጽዮን በእንባ ፊቷ እንደራሰ " ይሄ እኮ ለእኔ አይገባኝም ውለታህን እንዴት ነው የምከፍለው ? በሚል በስስት ታየው ጀመር... ዮሐንስ ምንም ባላደረገ ስሜት ሁኖ " ሁሉን ያደረገው ቅዱስ እግዚአብሔር ነው እርሱ እንደሰው አይደለም ልብንም ጭምር የሚያይ አምላክ ነው ስለዚህ የአንቺንም ልብ ክርስቶስ ተመልክቶታል" ብሎ በወንድማዊ ማፅናናት ካፅናናት በኋላ ወደ እናቷ ቤት ያቀናሉ...

ከሃሳብ መልስ እነ ጽዮን ቤት...

"ከዛም እሱ ቤት ከእናቴ ጋር ገባው ያቋረትኩትንም ትምህርቴንም ጀመረኩ አያትሽም ወደ ጤንነቷ ጠበል እየተጠመቀች ና ህክምናዋን እየተከታተለች ወደ ጤናዋ በእግዚአብሔር ሀይል ተመለሰች" በር ይንኳኳል የህይወት አባት ሶምሶን ነበር፤ የህይወት እናት ና አባት ጎልማሳ ወይም ከ30 - 40 በሚገኘው የእድሜ ክልል ላይ ይገኛሉ። ህይወት ወደ በሩ ለመክፈት እያቀናች " ቆይ እማዬ እኔ እከፍታለው" በሩ ተከፈተ... ሶምሶን በጎርናና ድምፁ " እንዴት ዋላችሁ ? ሰላም ለዚህ ቤት ....ህይወቴ ምን ሁነሽ ነው ለምንድነው ያዘንሺው ? በእጁ የያዘውን ፌስታል እየጣለ ልጁን ህይወትን እያቀፈ፤ ህይወት አባቷን ለማረጋጋት " አባ ተረጋጋ ምንም አልሆንኩም..ሶምሶን ቀጠል አድርጎ " የኔ እናት ምን ሁነሺብኝ ነው ሁለታችሁም እኮ እያለቀሳችሁ ነው ምነው አሞሻል እንዴ" ሚስቱ ጽዮን የተቀመጠችበት አጠገብ ለመስማት እያረፈ የሁለቱንም እጅ ይዞ እየጠየቃቸው፣ ባሏን ለማረጋጋት ጽዮን "አይደለም የኔ አባት እኔ እና አንተ እንዴት ለዚህ ክብር እንደበቃን ለልጃችን እየነገርኳት ስለሆነ ነው" የሰርጋቸውን ፎቶ በእጇ ይዛ እየጠቆመች ህይወት ፊት ለፊታቸው ስትቀመጥ ሶምሶን ትካዜ እየወረረው በምናቡ የማይጠፋውን ቀን እያስታወሰ...

ሱሰኛው ሶምሶን...

ዮሐንስ ከጓደኞቹ ጋር ከሰንበት ትምህርት ቤት ወጥተው ሲሄዱ ከቤተክርስቲያኗ ፊት ለፊት አንድ ክፉኛ የሚያስል ሰው ያያሉ፤ ከዛም ከዮሐንስ ጓደኞች አንደኛው " ዮሐንስ አየኸው ቆይ ቢቀርበትስ እንዲህ እስኪሆን ድረስ ለምን ያጨሳል ? በመናቅ ስሜት ... በመደነቅ ታለ ዮሐንስ "ከዚህ በፊት ታውቁታላችሁ" በማለት እሱ እንደማያውቀው ይጠይቃቸው ጀመር፤ ነገር ግን ሱሰኛው ሶምሶን እንዲድን የእግዚአብሔርን ፈቃድ እየጠየቀ ነበር፡፡ ሁለተኛውም ጓደኛ ቀጠል አድርጎ "አልፎ አልፎ እናየዋለን" የመጀመሪያው ጓደኛውም ደገፍ በሚያደርግ ሃሳብ " እኔ ምለው የሰው ልጅ የሚያስብ ህሊና አለው አይደል እንዴ ለምን እንዲህ ይዘቅጣል !" በመጠየፍ ስሜት እየተቆጣ፣ ዮሐንስ ንግግራቸውን ከሰማ በኋላ " ወንድሞቼ ማን ወዶ እጁን ወደ እሳት የሚልክ አለ ጴጥሮስ ጌታን የከዳው ህሊና ስላልነበረው ነው እንዴ ? ፍርሀት አሸንፎት ስላልበሰለ እንጂ... ለምንም ነገር መነሻ አለው ቆይ ወንድሜ የዚህን ሰው ችግር ለምን እንደሚያጨስ ቀርበህ ጠይቀኸዋል ? የመጀመሪያው ጓደኛም " አይ እኔ ፃዲቅ አይደለው" የተሳሳተ ንግግሩን ዮሐንስ ያቋረጠ "ፃዲቅ ለመሆን እኮ ምግባር ይቀድማል ውጤት ያለ ስራ እንዴት ይገኛል እንዲህ ከሆነ ክርስትና ገና አልገባንም ማለት ነው፤ አሁን ይህን ሰው ሂደን መርዳት አለብን" ሲል ከአንድ ጓደኛው በቀር ሌሎቹ እያጉረመረሙ ጥለውት የይምሰል ክርስትናቸውን በቀሪው ህይወታቸው ሊደግሙ በጎ ቀናቸውን ሸረው ሄዱ፤ ወትሮስ ለጥሬ ክርስቲያን መርጃ መንገድ ገንዝብ ና ገንዘብ ይመስለዋል እንጂ ጆሮ መስጠት ራሱን የቻለ መድኃኒት እንደሆነ

አይታየውም። ሶስተኛውም ጓደኛ "ተዋቸው መምህር አንድ ቀን ይገባቸው ይሆናል" በማለት ሊረዳው ይጥራል፣ ዮሐንስም " እሱማ አይቀርም ወንድሜ እኔን የሚያሳስበኝ ኑረን ነው ወይስ በሞት ስንጠራ ከረፈደ ነው የሚገባን እኛ ለመቅደሱ የቀረብን ሰዎች እስኪገባን ስንት የጠፉ ነፍሳት ማን ይድረስላቸው! ?" በቁጭት... " በል ለማንኛውም እኔ እና አንተ ለዚህች ነብስ ከእግዚአብሔር ጋር የምንችለውን እናድርግላት ውሀ ይዘህ ና" ብሎት ሲሄድ ዮሐንስ በሱስ ወደተጎዳው ወጣት ልጅ ተጠግቶ ያወጋው ጀመር፤ ዮሐንስ " ምን ሁነህ ነው ወንድሜ ለምን ራስህን ትጎዳለህ" በሱስ የተጎዳው ቀና ብሎ ዮሐንስን እያሳለ ይመለከተዋል። ዮሐንስም " እባክህ ወንድሜ እኔን እንደ ወንድምህ ማየት ትችላለህ" ውሀውን ጓደኛው ገዝቶ ይመጣል "ይኸው መምህር" ውሀውን እየሰጠው.. ዮሐንስ "በል እንካ ጠጣ ያረጋጋሀል፤ ሱሰኛው ሶምሶን ትን ሲለው ዮሐንስ አይዞህ እያለ እያረጋጋው እና እየደገፈው " ስምህ ማነው ወንድሜ" መረጋጋቱን ካየ በኋላ...ሶምሶን...ሶምሶን እባላለሁ" ይለዋል ውሀው ጠጥቶ ለመረጋጋት እየታገለ ፣ ዮሐንስም " እሺ ሶምሶን እኔ ዮሐንስ እባላለሁ እሱ ደግሞ ኤፍሬም ይባላል እና ሁለታችንም ወንድሞችህ ነን ምንም መፍራት የለብህም ንገረን ለምንድነው እንዲህ አይነት ህይወት ውስጥ የገባኸው ? በማለት በዝግታ ድምፅ ይጠይቀዋል። ሶምሶን እንባ ይቀድመውና ማልቀስ ይጀምራል ዮሐንስ እና ኤፍሬም በሀዘን እየተያዩ ሊያፅናኑት ሲሞክሩ ቀና ብሎ ታሪኩን ከጅምሩ ቤታቸው በሌላ መወረሱን ና እናት አባቱም በነበረባቸው የጤና እክልና የሁኔታዎች መደራረብ እንዲሁም የእድሜያቸው መግፋት ለህልፈት እንዳደረጋቸው ፣ እሱም ለእነሱ ብቸኛ ልጅ እንደሆነና ትምህርቱን አቋርጦ ጎዳና እንደወደቀ ይተርክለታል።

ዮሐንስና አፍሬም ነግሯቸው ሲጨርስ አብረውት እያዘኑ አቅፈውት ካፅናኑት በኋላ ዮሐንስም " በል ተነስ ወደ ቤታችን እንሄዳለን ከዚህ በኋላ ጎዳና መውደቅ መተኛት የለብህም" ሶምሶንም " አይ ወንድሜ ያ እንዴት ይሆናል በፍፁም ሸክም ልሆንብህ አልፈልግም" በማለት በማፈር ስሜት ይነግረዋል፤ ዮሐንስም "ተው እንደሱ አይባልም ከዚህ በኋላ እኔ ምልህን ነው እሺ ማለት ያለብህ እባክህ ወንድሜ ና አግዘኝ ወንድማችንን ወደቤቱ እንውሰደው" ሶምሶን የዮሐንስን አይን እያየ ይዘውት ወደ ዮሐንስ ቤት ይሄዳሉ።

ዮሐንስ ና ሶምሶን ሱባኤ ይዘው...

ሶምሶን ዮሐንስን በመመልከት ጥያቄ ይጠይቀዋል " መምህር ... ዮሐንስ የሶምሶንን ጥሪ በመቀበል " አቤት ወንድሜ " ሶምሶንም " እግዚአብሔር ይቅር ይለኝ ይሆን ? ዮሐንስም የሶምሶንን ሃሳብ በመረዳት " አዎ ወንድሜ እግዚአብሔር ይቅር ባይ ነው" ሶምሶንም በመቀጠል " መምህር ግን እግዚአብሔርን በብዙ በድዬዋለሁ እኮ ! ዮሐንስ ፈገግ በማለት " ከመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል የሉቃስ ወንጌል 15÷17 የተፃፈውን ወርቃማ ታሪክ በማውሳት ሶምሶንን ልቡን ዕረፍት እንዲሰማው

በማድረግ ሲያፅናናው ሶምሶን ከአይኖቹ ትኩስ እንባ ዱብ...ዱብ እያለ ጉንጮቹን ያርሰው ጀመር፤ ይህም ከሱሱ እንዲያገግም ሱባኤ በያዙበት ወቅት ነበር።

ሰንበት ትምህርት ቤት !!!

ሰንበት ትምህርት ቤት አዳራሽ ሰንበት ተማሪዎች ተቀምጠው እያወሩ ዮሐንስ ሶምሶንን ይዞ ሲገባ ሶምሶንን በበፊት ማንነቱ የሚያውቁት ሲያጉረመርሙ ዮሐንስ ወደ አትሮንሱ ሂዶ ከአማተበ በኋላ "ስታመነዝር አገኘናት በድንጋይ ተወግራ ትሙት ብለው አንዲትን ሴት ወደ ጌታ አመጡለት ጌታም መልሶ ጠየቃቸው ከእናንተ መካከል ሀጢአት የሌለበት ቢኖር ይህችን ሴት አስቀድሞ ይውገራት ሲላቸው ሁሉም ድንጋያቸውን እየጣሉ አንድ አንድ እየሆኑ ሄዱ ጌታም ከሴቲቱ እና ከእርሱ በቀር ማንንም ባላየ ጊዜ ወደ ሴቲቱ ዞሮ አንቺ ሴት ከሳሾችሽ ወዴት አሉ ሲላት እርሷም መልሳ ጌታ ሆይ አንድስ እንኳ ስትለው እንኪያስ እኔም አልፈርድብሽም ደግመሽ ኃጢአትን አትስሪ ብሎ በነፃ አሰናበታት በዚህ ውብ ታሪክ ላይ እግዚአብሔር አለመፍረድን በሚገባ አስተምሮናል አሁንም ደግሜ እጠይቃችኋለሁ እዚህ ከተሰበሰብነው ውስጥ ሀጢአት ያልሰራን ካለን አስቀድመን በሀሜት ድንጋይ ይህ ወንድማችንን እንውገረው ...አለ ? ያልበደለ..እህ. ታዲያ ለምን እርስ በእርስ እንጨካከናለን ሁላችንም እኮ የአንድ አባት ልጆች ነን ብቻችን የምንወርሰው እርስት መንግስተ ሰማያት የለንም ወንድሞቻችንን እና እህቶቻችንን ትተንስ መች ፀልየን እናውቅና ፣ አባታችን ሆይ ብለን መፀለያችን ካልቀረ ወገኖቼ እኔ ታናሽ ወንድማችሁ እለምናችኋለሁ በክርስቶስ ፍቅር ፍፁም እንዋደድ" ንግግሩን ሲቋጭ አብዛኛው ሰንበት ተማሪ ልቡ ተሰብሮ እያነቡ ሶምሶንን ተነስተው ይቅርታ እየጠየቁት ያቅፉት ተያያዙ..

ከሀሳብ መልስ አሁን ላይ ...

አባት ሶምሶን እያወራ ህይወት እንባዋን እየጠረገች ሶምሶን "ከዛ እቤቱ ካስጠጋኝ በኋላ ከእናትሽም ጋር ተዋደድን መዋደዳችንን ቀድሞ ያውቅ ነበርና ሁለታችንንም አንድ የንስሐ አባት አሲዞን እኔም ራሴን ስችል እናትሽም በተማረችበት ስራ አግኝታ ራሷን ከቻለች በኋላ እሱን አማክረን በቤተክርስቲያን ስርዓት ተጋባን ከዚህ በኋላ ያለውን አንቺም ታውቂዋለሽ ህይወቴ የኔ ልጅ" ህይወት እንባዋን እየጠረገች ስልክ ይደወልላትና ተነስታ ልብሷን ቀይራ ነጠላ እና ቀሚስ አርጋ ቤተሰቦቿን ተሰናብታ ወደ ተደወለላት ታቀናለች። ጻዲቁ እብድ በሃሳብ ማዕበል :-

እውነት....እውነት ! እውነት አርግዛ ወለደች
ጠያቂ ብታጣ በውሸት ታረሰች
ኧሀሀሀ....እህህህህ "በምፀት ይስቃል፤"
ስጋውን የበላ ደሙን የጠጣ የዘለዓለም ህይወት ስለሚኖረው
የሚል ሰባኪ ከቃል አልፎ በተግባር ካልኖረው
የመምህርነት ቀሚሱ በነጭ በጥቁር በዓይነት በዓይነቱ
ከምእመናን እጅጉን ወርዶ ከከሳ እምነቱ
ህእ.... መቼ ተኖረ
ስጋ ከከበረ
ዓለምን መውደድ ደዌ ነው
ዓለምን መናቅ መድኃኒት አለው
ወንድሞቼ ሆይ ዓለምንና በዓለም ያለውን አትውደዱ
ብሎ የሚያስተምር ማስተማሩ ስለገንዘብ ከሆነ የግዱ
እህ..... መቼ ተኖረ
ስጋ ከከበረ " ህይወት የጻዲቁን ንግግር ቤተክርስቲያን እየሳመች
ውስጧ ሲሰርፅ ተሰማት፤ ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት ስብሰባ እግሮቿን
ወደ ውስጥ ሰደደች።" ጻዲቁ እብድ ቀጥሏል :-
እውነት ... እኮ እውነት አዎ እውነት አርግዛ ወለደች
ጠያቂ ብታጣ በውሸት ታረሰች

የሰንበት ትምህርት ቤት ስብሰባ...

የሰንበት ትምህርት ቤት የአመራር መሰብሰቢያ ክፍል ውስጥ የሰንበት ት/ቤቱ ልብሰ ስብሐት ጠፍቶ አብዛኛዎቹ በንዴት ሲጨቃጨቁ እርስ በእርሳቸው መደማመጥ ሲያቅታቸው ሰብሳቢው " እባካችሁ እንደማመጥ እንደማመጥ እንጂ እኔ ምልሽ ህይወት ..ህይወት" ህይወት ከገባችበት የሃሳብ ውዥንብር እየተመለሰች "አቤት ጠራኸኝ" ሰብሳቢው "አንቺስ ምን ትያለሽ ? " ህይወት "በምን ጉዳይ ? " ሰብሳቢው "ህይወት ምን ሁነሻል ይሄ ሁሉ ሰዓት ሁላችንም ስንወያይ የነበረው ስለጠፉ ልብሰ ስብሐቶች ነው እኮ ! " ህይወት ቀጠል አድርጋ "እ......ይገርማል ለካስ ልብስ ከሰው በላይ አስፈላጊ እንደሆነ አላውቅም ነበር ! ሰብሳቢው "ማለት ምን እያልሽን ነው አልገባኝም ህይወት መልሳ " አዎ እኔም እንዲህ አይገባኝም ነበር እኔም ምለው ለምንድነው ይህን ሀላፊነት የተቀበልነው ? ከአመራሮች አንደኛው "ሀሀሀ" በሹፈት እየሳቀ " የተሰጠንን ሀላፊነት በሚገባ ልናገለግል ነዋ" ከፊሉ ይስቃል ይጠቋቆማል፤ ህይወት የአመራሩን ሁኔታ ካየች በኋላ " እህ....ልናገለግል ቁስ ወይስ ሰው እስቲ ልጠይቃችሁ ከዚህ ሰንበት ትምህርት ቤት ስንት አባላት ጠፍተዋል ወይም እንደዚህ ቀለል ላድርገው በዓመት ከዚህ ሰንበት ትምህርት ቤት ስንት አባላት ይወጣሉ ፣ በወራት ፣ በሳምንታት ፣ በቀናት ፣ በሰዓታት ፣ በደቂቃ ፣ በአሁኗ ሰከንዶች ? እንዲህ አውቀናል የምንባል ሰዎች የሚያምር ጭቅጭቅ በምናደርግበት ሁኔታ ውጪ ያሉት አባላት ልባቸው ምን እንዳዘለ ምን አይነት ሁኔታ ውስጥ እንዳሉ የሚያውቅ አለ ቆይ ! የጠፉትስ ትናንት ከአንተ ፣ ከእናንተ ፣ ከእኔ ጎን አብረው ተቀምጠው ፣ ቁመው ይማሩ ይዘምሩ የነበሩ አባላት ዛሬ የት ናቸው ፣ የትስ ወድቀው ይሆን ፣ ስንቱስ ተስፋ ቆርጠው ይሆን ፣ ስንቱስ የማይሆን ህይወት ውስጥ ገብተው ይሆን ?

ሰብሳቢው ሊያቋርጣት እየጣረ " እ ህይወት እሺ... ህይወት የሰብሳቢውን ንግግር በመግታት " አታቋርጠኝ አልጨረስኩም! የእኔ ፣ የእናንተ እህት ወንድሞች የት ናቸው እ...ንገሩኛ የት ናቸው ? ምነው ይሄ አያስቅም በሉ ሳቁ እንጂ !!! "እርስ በእርስ በኃፍረት እየተያዩ" ዛሬ የእኔ ፣ የእናንተ ታናናሽ እህት ወንድሞች አፍላ ፍቅር ጀምረው ስንቱስ በዝሙት ወድቀው ይሆን ?ለእነሱ የሚደርሰው ማነው እ ? ምነው እንዲህ ንብረት ሲጠፋ የተንገበገብነውን ያህል ነብሳት ሲጠፉ ምነው ግድ አልሰጥ አለን ! ምነው አላሳዘነን ! ምነው ምህላ ይዘን አላለቀስን ! ለነገሩ በየትኛው ጊዜያችን አይደል የዓርብ ፀሎት እንኳ ለአቴንዳንስ እየገባን ! ወደን ሳይሆን አገልግሎት ለመሰለፍ ስንል የግዳችንን እየፀለይን እንዴት ብለን እናልቅስ ቢሮ ተሰጥቶ የለ... ማን በቀልድ ፣ በወሬ ያድምቀው ? ማንስ ያሽካካበት ? እኛ አብነት መሆን ሲገባን እንደ አይሁድ የቤቱ ዘመን ሻጭ እና ለዋጮች ሁነን እንቅር ! ቆይ መቼ ነው ማገልገል ምንጀምረው ጌታ ለፍርድ ሲመጣ ጌታ ሆይ ይህ ሁሉ ልብሰ ስብሐት እና ንብረት አለን ብለን ልናሳየው ነው ? ለባሹ ከሌለ እዚህ ሳይገባን የተቀመጥነው አቀያይረን አማርጠን ከመልበስ ውጪ ምን ያደርጋል ! ዘመን ከሚገታው ልብስ ይልቅ ዘመን የማይገታው ለዘለዓለም ስለተፈጠረው የሰው ልጅ ብናስብ ፣ ብንጨነቅ መልካም ነው ያኔ እግዚአብሔርም ከእኛ ጋር ይሆናል !!! ብላ ልቶጣ ስትል ፀሐፊው "እና በጸሎት የተከፈተ መርሐግብር ረግጠሽ መውጣትሽ ነው" ህይወት በግርምት ፈገግታ :-

"በጾሙ ጨፍረው እንዳሻቸው እየበሉ
ደግሞ ቀን ቆጥረው ሊፈታ ነው ይላሉ" ብላ በሩን ስትከፍት ሰብሳቢው "ህይወት ቆይ... ወዴት ነው" ተነስቶ ከወንበሩ እየጠየቃት ህይወትም "ራሴን ፍለጋ" ብላ ስተወጣ ሁላቸውም አፍረው በዝምታ ይዋጣሉ።

ጻዲቁ እብድ ና ሕይወት...

ከሰንበት ትምህርት ቤቱ አዳራሽ ወጥታ የቤተክርስቲያኑን አጥር ተሳልማ ወደ ጻዲቁ እብድ ማዶ ታቀና ጀምር፤ ህይወት ወደ ፃዲቁ እብድ አጠገብ ስትደርስ ፃዲቁ እብድም ከራሱ ጋር የዘውትር ንግግሩን ገጥሟል :-

"ተይ ነብሴ ግድ የለም መዝኚ
በቃሽ ዓለምን አትመኚ
እውነት...አዎ እውነት እውነት አርግዛ ወለደች
ጠያቂ ብታጣ በውሸት ታረሰች" አጠገቡ ስትቆም ጻዲቁ እብድ ቀና ብሎ ሲመለከታት ህይወት በፈገግታ "መመዘን እፈልጋለሁ" እየተብሰለሰለ ትኩር ብሎ ሲያያት ፊትለፊቱ በመካከላቸው ሚዛኑ ሁኖ ከእሱ አንፃር ተቀምጣ "አዎ ነብሴ ወይስ ስጋዬ የቱ ነው ሚዛን የሚደፋው ማወቅ እሻለሁ" አይን ለአይን እንደገጠሙ...

አለቀ ግን እንዴት.....

መዝሙረ ዓለም

ምግባሬ ልል የእርሱ ደቀመዝሙር
መኖር የሌለኝ የእንዲህ ይላል ክምር
ውስጤ ጠቁሮ የጌታ ነው ብባልም
መቼ ታከተኝ መዝሙረ ዓለም ስደግም
መዝሙረ ዓለም ንግግሬ
የውሸት አኗኗሬ
መዝሙረ ዓለም ምኞቴ
ክርስቶስን የገፋው ቤቴ
መዝሙረ ዓለም መንገዴ
ቤተክርስቲያን ስሄድ የግዴ
መዝሙረ ዓለም ህሊናዬ
ሳስብ ምድራዊ ሰማዩን ጥዬ
መዝሙረ ዓለም ልቤ
ያተምኩ ኃጢአትን ስቤ
መዝሙረ ዓለም እግሬ
የሮጠ ከክፉ ግብሬ
መዝሙረ ዓለም እጄ
የከፈተ ለኃጥእ ደጄ
መዝሙረ ዓለም ሆዴ
ያለጾም ኑሮ በሁዳዴ
መዝሙረ ዓለም ጉልበቴ
ለሰይጣን ሲሆን ስግደቴ

መዝሙረ ዓለም ዓይኔ
ዝሙትን ሸጦልኝ ለእኔ
መዝሙረ ዓለም ጆሮ
የዘፈን የኃሜት እሮሮ
መዝሙረ ዓለም ምላሴ
ስታለያየኝ ከነብሴ
መዝሙረ ዓለም አፍንጫዬ
የከረፋው ልማዴን ይሁን ብዬ
መዝሙረ ዓለም የእኔስ መዝሙሬ
ፀንሼ የወለድኩት ሁኗል እኩያ አጋሬ

ዝምታ

ግን ለምንድ ነው
መጠይቁ ምድራዊ የሆነው
ምንድን ያሰኘኝ
ፈውስ ላይሆነኝ
ዝምታዬ ሀገር
የመታደስ ቀመር
የኔ መፅናኛ
ፅኑ መታመኛ
ልቅሶ ደስታዬ
ድብቅ ዋሻዬ
አንቺ ነሽ ዋስትናዬ
የመኖር ጉያዬ

ውሀ እና እሳቱ

ዓለም ያሰከረው
ግሳቱ ለቅሶ ነው
ፍቅሩም የደበዘዘ
በሃጢአት እንደደነዘዘ
ተአምር ይጠብቃል
ሰው ይናፍቃል
ወይኩን ብሎ
ልማዱን አባብሎ
ውሀ እና እሳቱ
ምርጫው ሁኖ መብቱ

የታመነ ነው

"ኃጢአታችንን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃ ሁሉ ሊያነጻን የታመነ እንደሚመለከትህ (1ኛ ዮሐንስ 1÷9)
"ሰዎች እንዴት እንደሚያስቡህ እየተብሰለሰልክ ከምትኖር ይልቅ እግዚአብሔር አንተን እንዴት እንደሚመለከትህ አስብ ፤ ለአንድ ቀን ለዛውም ከአንድ ቀን ለሰዓታት ፣ ከሰዓታትም ለደቂቃዎች ፣ ከደቂቃዎችም ደግሞ ለሰከንዳት ያስከፋኸው ሰው ምን ያህል ቀናት ፣ ወራት እንዲሁም ዓመታት አንተን ይቅር ለማለት እንዴት ደጅ አስጠንቶህ ይሆን ? ደግሞ የዘጋህ ወይም ያኮረፈህ ባልተረጋገጠ ነገርም ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ከአፈር ያበጀህ እስትንፋስን እፍፍ.. ያለብህ እስካሁኗም እድሜህ ስትበድለው ሁሉን ማድረግ እየቻለ አትረባም ፣አጠቅምም ፣ ከዚህ በኋላስ የአንተ ነገር በቃኝ ብሎ መቼ ፊቱን አዞረብህ ? ይኸው ትናንትናን አሳልፎህ ዛሬ ላይ እያኖረህ አይደል ? በኃጢአት እንኳ እያሳዘንከው አንተን አይደል በንስሐ ትመለሳለህ ብሎ ሚጠብቀው ? ምሽቱን አንግቶ አዲስ ቀን እያሳየህ አይደለምን ? ይኸውልህ እግዚአብሔር ድንቅ ነው ከሚባልበት ነገር አንዱ እኛን ይቅር ማለቱ ብቻ ከመሰለህ ተሳስተሀል ፤ ምክንያቱም የአባትነት ግብሩ እኛን መማሩ ነው። ነገር ግን ከሁሉ በላይ የሚደንቀው እኛ የልጅነት ድርሻችንን ሳንወጣ ይቅር በለን ሳንለው በይቅርታ እያለፈ እድሜ ለንስሐ መስጠቱ ነው።
ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዲህ ይለናል :-"እግዚአብሔር ከአባት ፣ ከእናት ፣ ከጓደኛ ወይም ሌላ ማንም ሊወደው ከሚችለው በላይ እና እራሳችንን መውደድ ከምንችለው በላይ ይወደናል"ስለዚህ ደግሜ እልሀለው :- "ሰዎች እንዴት እንደሚያስቡህ እየተብሰለሰልክ ከምትኖር ይልቅ እግዚአብሔር አንተን እንዴት እንደሚመለከትህ አስብ።

ፍቅር የለው ታሪኬ

ዛሬን ማሳየትህ ብቻ ፍቅርህን ይገልፃል
አንደበቴስ ችሎ እንዴት ቃል ይደረድራል
እንጃ ሁለን እያወክ ፊትህ ይበራል
እንደ ኃጢአቴ ቢሆንማ መሞትስ ይበቃኛል
እንጃ ግራ ሆኖብኛል
ከሁሉ ይልቅ ዝምታህ ያስፈራኛል
እንጃ ለምን ብትለኝ ደግሞ አምላኬ
ለፍቅር መሆኑን ስለማቅ ፍቅር የለው ታሪኬ

የእኔ አገልግሎት

ጥጋብ እጅግ በጣም ክፉ ነው የሰዶም ሰዎች የተቀጡት በጥጋብ ነው፤ ዝሙትም ሚወለደው ከምንድነው ቢሉ ከጥጋብ ነው። "ብዝኃ ዕፀው ያስተናድዶ ለእሳት ወብዝኃ መብል ያስተናድዶ ለፍትወት" የእንጨት ብዛት እሳቱን በደንብ ያነደዋል፤ የመብል ብዛትም ዝሙትን በሠውነት ውስጥ በደንብ ያቀጣጥለዋል። እንጨቱን ስንጨምር እሳቱ እንደሚጨምረው ሁሉ መብል ስንጨምርም ዝሙት ይጨምራል። ከተራበ ሰውነት ዝሙት አይገኝም፤ ዝሙትስ የሚገኘው አርፎ ከሚበላ ከሚጠጣ ሠውነት ነው። እየበላ ከማይሰግድ ከማይፆም ሠውነት ያለመጠን ከሚበላ እንዲህ ያለ ሰው ዝሙት ይሠለጥንበታል። እንግዲህ ምዕመናን ከእንዲህ አይነቱ በእውነት ልንጠበቅ ዘንድ መጾም ያስፈልጋል ይቆየን፤ ምዕመኑ እኔም መምህሩ ሲጨርሱ አጨበጨብን እልልም አልን፣ ነገር ግን አንድ ልማዴ ታወሰኝ መክሰስ ሲቀርብኝ እናት እና አባቴ ማመናጭቃቸው ጊዜያቶች ምግብ ቶሎ ካልሠጡኝ እንዴትስ ከፍ ዝቅ አድርጌ ምናገራቸው ንግግሬ ምንም አይደል ሀጡአቴ ትዝ አለኝ። ስብከቱስ ለእኔ አዲስ አልነበረም ምክንያቱም የሰንበት ትምህርት ቤት መዘምራን እንዲሁም ቀዳማይ፣ካላይ ብዬ የተማርኩ አዎ ሰንበት ተማሪ ነኝ !። እናትህና አባትህን አክብር ባለ ጌታ ፊት ምበድል በምድር ደግሞ እናት እና አባቴን የምዘልፍ እድሜዬ የቀደመኝ ሰንበት ተማሪ ነኝ። ትናንት ማለዳ የቤተክርስቲያናችን ዋና አስተዳዳሪ ስብሰባ ጠርተው ነበር፤ እኔም ሰንበት ትምህርት ቤቱን ወክዬ ተሰበሰብኩ። ለመናገር ተራዬ

ሲደርስ አንድናገር "አባ" እድል ሠጡኝ፤ ጉሮሮዬን አፀዳሁና አስከትዬ "አባታችን እግዚአብሔር ይስጥልኝ በእውነት በእነዚህ ሊቃውንት በእርሶም ፊት እናገር ዘንድ አግባብ አይደለም።" እፁብ ድንቅ በሆነ የሽንገላ ምላሴ የሌለኝ ትህትናዬን ማሳየት ተያያዝኩ፤ ከዛማ ምን ይነገራል የሆነው እየሆነ የውሸት ህይወቴ ይኸው ዛሬም አለ። ግንኙነትም ክፍል ነኝ ሴት ማሽኮምም ስልኳን ለማግኘት መዝገብ ማገላብጥ እገሊት እምነት ቀየረች እገሌ እንዲህ ሆነ ስባል ድሞም እኮ እነሱ ችግር ነበረባቸው የምል ተጠያቂ ሳይሆን ጠያቂ የሆንኩኝ አዎ ሰንበት ተማሪ ነኝ። እኔ ምልሽ አዲስ የገባውን ሰንበት ተማሪ አየሺው አዎ በእናትሽ አያምርም? በጣም እንጂ እያልኩ ከትናንቱ ዛሬ ካለው ቋቁንጅናን
ማወዳድር እኔማ ሰንበት ተማሪ ነኝ።መዝሙርም ክፍል ነኝ ድምፄ ካማረ መዝሙሩን ሳስጠና በዘፈን ቅላፄ ከላይ ከላዩ የማበዛ በአይኔ ምሽከረከር ወደ ተሽፋፈኑት ፍለጋ ሚማረኩ አንስት ቁጥራቸው እንዲበዛ፣ በአትሮንሱ ፊት የምቆም በቤተክርስቲያን ግቢ ቀሚስ የማስጠብብ ሰውነቴም እንዲታይ ፓሪም የማስቀድድ መዝሙርም አስጠኚ አባል የሆንኩ እኔስ ሰንበት ተማሪ ነኝ።ስነስርዓት ክፍልም ነኝ ፀጉራቹን ሸፍኑ ወንዶች ተቆረጡ ጥፍራችሁን ሴቶች አታሳድጉ የምል የራሴን ፀጉር ቀለም ለማስቀባት በሴትነቴ ጥፍር ለማስተከል የውበት ሳሎን ቀጠሮ የማሲዝ በወንድነቴ በስታይል ለመቆረጥ ደና ፀጉር ቤት
ጠቁሙኝ የምል የሠውን መመለስ ሳይሆን ቅድሚያ ገፅታ የሚል መፈክር የያዝኩኝ መንክር ሰንበት ተማሪ ነኝ። ትምህርትም ክፍል ነኝ፤ ተቅለስላሽ እባብ ስንቱን በፖለቲካ ወሬ ነድፌ ዘረኛ ያደረኩኝ"ባልንጀራህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ" ብሏል እኮ ጌታ ብዬ ወተት መሣይ ነገር ግን በጎስነት ቀንበር የአባሉን ልብ በቅቤ ንግግር አላውሼ የምግት በየስብሰባው እንዲህ አስበናል እንዲህም ታቅዷል ብዬ የምፎክር ቀኑ ሲደርስ ማምለጫ ምክንያት ማሠማ በግምገማ ወቅትም ይሄን ያህል ዲያቆን እንዲማር እንዲፈራ አድርገናል የምል፣ ዝናም እየመታቸው ውርጩን ታግሠው ቦታ እየተነፈጉ ተምረው ዲያቆን ቢሆኑ የእግዚአብሔርን ቸርነት ለራሴ ወስጄ ለሪፖርት ማድመቂያ የማቀርብ ኧረ እኔማ ሰንበት ተማሪ ነኝ። ለጠፋው ግድ የማይሠጠኝ ትናንት ምድብ ያስጠናሁት ልጅ ፑል ቤት ለፑል ቤት ከሱስ ወደ ሱስ ሲናወጥ ማይሰማኝ፣ ስለማይሠማ ነበር እንዲህ የሆነው እያልኩ ሊጠፋ ያለ ነብስ እያለ እኔ ግን ነጭ ልብሰ ስብሐት ለመልበስ የምጣላ

ጥንግ ድርብ በነጭ ሱሪ ጫማዬን ክሬም አስቀብቶ በባእላት ከመታየት ውጪ ተኩላ ሊበላ ያለውን ዓለም ተሰፋ አስቆርጣ የወሠደችውን የመመለስ ሀዘኔታ የሌለኝ እዋ ሰንበት ተማሪ ነኝ። በእኔ ምግባር ሰንቱ ሀይማኖቱን ቀይሮ ይሆን? ሰንቱስ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶን ጠልቶ ይሆን! ንብረትም ክፍል ነኝ፤ የሰንበቱ ንብረት ተቆርቋሪ እቃ ሲጠፋ ምንገበገብ ሟች ዳሩን ጠባቂ፣ የመዘመራኑ ልብሰ ሰብሐት ሲጎል አባሉን በቁጣ በሰድብ አምጡ ብዬ ማሰሰ ዘማርያኑ ከአይን ሲርቁ መምጣት ሲያቆሙ እነሱን ፍለጋ ለመውጣት እግሬ ሚተሳሰር ሰራው የግንኙነት ክፍል አይደል የምል ቅርሰ አሰመዝጋቢ እኔማ ሰንበት ተማሪ ነኝ። በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ሊያሰቀድሰ የመጣውን ሰው ቀልብ የምገፍ እያሰቀደሰም ደክሞት ሊቀመጥ ሲል ተነሰ እንዴት ትቀመጣለህ ዛሬ ነው ምትመጣው እሰከዛሬ የት ነበርክ/የት ነበርሸ እግዚአብሔር ማያሣያቸውን አይነት ፊት ማሣይ ማዕተብ ያሰርኩ መናፍቅ ሁኛለሁ። ሰንት ጊዜ ሆነህ ? ሰንበት ትምህርት ቤት ከገባህ ብዬ ሰጠየቅ እ ! 10 ዓመት ፣ 15 ዓመት አይሆነኝም ብለህ ነው፣ ኧረ እኔ ከልጅነቴ ጀምሮ ነው የገባሁት ብዬ በኩራት የምመልሰ ልብሰ ሰብሐት፣ነጠላዬ ውሰጥ ሀጢአቴን ምደብቅ በሰው ሀጢአት እየተረባረብኩ የምፈርድ በየሶሻል ሚዲያው የእገሌ ጉድ ተዘረገፈ የእገሊት ቅሌት ተዘረገፈ የሚል ቪዲዮ ሳይ በደሰታ፣ በጉጉት ለማየት የምቸኩል፣ ራሴን ምፅድቅድቅ አድርጌ እንደ ፃድቅ ራሴንም ቆጥሬ ከፃድቃን ጎራ መመደብ የምፈልግ የማቱሳላን እድሜ የምሻ ነገር ግን ምግባሬ የሶሳቱን የፌያታዊ ዘየማንን ታክል የማትሞላ ኧረ እኔስ ሰንበት ተማሪ ነኝ።ቢገባኝማ የእኔን ሀጢያት የሸፈነልኝ ቸሩ መድኃኔዓለም ነበር፤ ገላዬ ቢቆሸሸ ገላይንም ባልታጠብ ሰውሰ ባራቀኝ በተፀየፈኝ ኑሮ፣ የሰጋዬ ቆሻሻ የሚቀርቡኝን እንዲህ ሊያሸሸ ከቻለ፣ እንደ ውሀ የተጋትኩት ነብሴን ያሰጨነቃት እኔ የማቀው ሌላ ሰው የሚያቀው እግዚአብሔርም የሚያቀው ሀጢአት ፣ እኔ የማላቀው ሌላ ሰው የሚያቀው እና እግዚአብሔር የሚያቀው ሀጢአት፣ እኔም የማላቀው ሌላም ሰው የማያቀው እግዚአብሔር ብቻ የሚያቀው ሀጢአቴ መሽተት ቢጀምር ወዳጅ ያልኩት ሸሽቶ በሄደ ዘመድም በጠላኝ ከሩቅ ቦታም ሁነው ያዩኝ ከዓለም ዳርቻ

 በሽሹ ሰለኃጢአቴም ሽታ ብለው እንደ አይሁዳውያን በመንፃት ሥርዓት ንስሐ በገቡ ነበር። አባ ጊዮርጊስ ዘጋሰጫ እንዲህ ይላል "እግዚአብሔር ሰለድንግልናው ከሚመካ ፃድቅ ሰው ይልቅ ሰለ ሀጢአቱ የሚያለቅሰን ዘማዊን ይወዳል"

ወንድሜ የአንተሰ አገልግሎት እህቴ የአንቺሰ አገልግሎት ምን አይነትሰ ሰንበት ተማሪ ናችሁ? መልሱን ለእናንተው ልተወው እኔን የወደኩትን ግን በፀሎት አሰቡኝ።

የእኔ አገልግሎት ይቀጥላል...

ስሜታዊ አገልጋይ

"ድግስ ደግሶ በድግሱ ላይ ያልተገኛቹለትን እግዚአብሔር እንዴት እናንተ በምፈልጉት ጊዜ እንዲገኝ ትሻላችሁ"

ክርስቶሳዊ ትህትና የሌለው ህንፃ ፣ ህንፃ ብቻ የሚል የቤተክርስቲያን አስተዳደር ሰንበቴ መዘከር ዘክሮም መሄድ ብቻ ንሰሐ የማይገባ ስጋ ወ ደሙን የማይቀበል ምዕመናንን ያፈራሉ።

ቁርባን እንዲሁም መንፈሳዊ የምግባር ልማድ የሌለው የሰንበት ትምህርት ቤት አመራር በክርስቶስ ክቡር ሰርግ ላይ ታድመው ብቻ የሚመለሱ ፣ ሕይወት ክርስቶሳዊ የሌላቸው ፣ ልብሰ ሰብሐት በመልበሳቸው ብቻ ክርስቶስን ያገኙ የሚመስላቸው ፣ በወረብ በመዝሙራቱ ሀጢአታቸው የሚሰረይ የሚመስላቸው ትውልድ ፣ የኮርስ ሰርተፍኬት ጥርቅም እንጂ የተማሩትን የማይኖሩት እንዲሁም ደግሞ የሚማሩት ትምህርት በአብዛኛው theory ወይም በቃል ብቻ ስለሆነ የማይኖሩትን ቃለ እግዚብሔርን የተሸከሙ የእዳ ክርስቲያን የሆኑ አባላትን ያፈራሉ።

ስሜታዊ የሆነ የቤተክርስቲያን ማህበር በአላት ፣ ንግስ በደረሰ ቁጥር ክርስቶስ ትዝ የሚለው ወጣት እንዲሁም ምዕመናን ያፈራሉ፤ ባንዲራ መስቀል ፣ ምንጣፉ ማንጠፍ እንጂ ምንጣፉን ለማንጠፍ የሚያደርገው የወገብ መጎንበስ በላይ ልቡ በንሰሐ መሰበሩ ክርስቶስን እንደሚያስደስተው የማያውቅ ፣ ጉዞ በመጓዙ ብቻ ሀጢአቱ የሚሰረዝለት በማወቅ ወይም ባለማወቅ የማይዘበትበትን ቅዱስ እግዚአብሔር ላይ ብልጣ ብልጥ ለመሆን የሚሞክር ትውልድን ይፈጥራሉ።

የቅዱሳን አባቶች ወርቃማ አባባሎች

"በልቡ እግዚአብሔርን የያዘ ሰው ሕግጋቱን መፈጸም ይችላል፤ ነገር ግን በከንፈሩ ብቻ ጌታ ሆይ የሚል ልቦናው ተጠራጣሪ ስለሆነ የእግዚአብሔርን ሕግ መፈጸም አይችልም"

እረኛው ሄርማን

"ወንድሞቼ በመሰመሩ መጨረሻ ላይ በደረሰኩ ጊዜ ፍቅራችሁ ስለጎዳኝ ፈራሁ እናንተም የሕይወቴን ጉዞ ዳግመኛ እንድሮጥ ፈለጋችሁ"

ቅዱስ አትናቴዎስ

"የሰው ልጅ እጅግ ጥቂት ምሕረትን አድርጎ እጅግ ብዙ ምሕረትን ከእግዚአብሔር ያገኛል"

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

"በጸሎት ነፍስ ከእግዚአብሔር ጋር ተዋሕዳለች የኔነቱን ምሥጢር ታያለች ደስ እያላት ሥራዋን ሁሉ በርሱ ብርሃን ታያለች የሚያሸበርቅ የጌታን መልክ በማየት ታበራለች"

አረጋዊ መንፈሳዊ

"ፈጣሪዬ ሆይ በፊትህ የምንቀጠቀጥና ኃይል የሌለኝ ባሪያህን አንተ አሰበኝ፣ በሞገሰና በቸርነትህ አትለየኝ"

አቡነ ቄርሎስ

"ሁላችንም ኃጢአን፣ ተላላፊዎች ሆነናልና ኃጥኡን አትጥላው፤ ግድ ካለህሰ ለእርሱ አልቅስለት፤ ለነፍሱም ጸልይለት"

ቅዱስ እንጦንስ

"መከራችሁ እንደማያልቅ በማሰብ ራሳችሁን አታሰጨንቁ! እግዚአብሔር መጽናናትን ይልካል። በሚጨመር መከራ ውሰጥ መጽናትን መማር አለባችሁ! ይህ ሲሆን ነፍሳችሁን ታድናላችሁ ሌሎችንም ትረዳላችሁ"

ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ

"የሰውን ልጅ በሩህሩህነት አሸንፈው ቀናተኛውን በመልካምነትህ እንዲደነቅ አድርገው ሁሉንም ሰው ውደድ ነገር ግን ከሁሉም ሰው ርቀትህን ጠብቀህ ኑር"

አባ እንጦንስ

"ከኃጢአት ቀጥሎ ኃፍረት አለ ፣ ከንስሓ ቀጥሎ በጌታ የሆነ ደስታ አለ፤ ነገር ግን ሰይጣን ይህን ቅደም ተከተል አዛብቶብን በኃጢአት ስንደሰት በንስሓ እናፍራለን"

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

"ነጋዴ በሚነግደው ነገር ለውጥ ካላመጣ (ካላተረፈ) ለምን ይነግዳል? አንተስ በመንፈሳዊ ሕይወትህ ለውጥ ካላመጣህ ለምን ክርስቲያን ነኝ ትለኛለህ?"

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

"ካለ መኖር ወደ መኖር መምጣታችን የእግዚአብሔር የመጀመሪያው ስጦታ ነው
ይህን የምናውቀው በቅዳሴ ጎርጎርዮስ ውስጥ " እኔ ሳልኖር አንተ አበጀህኝ! "
ተብሎ የተጠቀሰውን ቃል ስናስታውስ ነው። እግዚአብሔር ይህን የሕልውና ስጦታ ባይሰጠን ኖሮ ምንም አልነበርንም። ይህ በመሆኑም እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠን የመጀመሪያ ስጦታ እኛን መፍጠሩ ነው ።"

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ

የንስሀ አባት ማለት እርሱን ስትመለከት እግዚአብሔርን እና ትዕዛዛቱን የምታስታውስበት ሰው ማለት ነው"

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ